# ገድለ ክርስቶስ ሠምራ

## ግእዝና አማርኛ

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

አ ዲ ስ አ በ ባ

፲፱፻፺፱ ዓ/ም

# መ ግ ለ ጫ ።

እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ ለመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ ለአዳም ፡ በሰጠው ፡ ተስፋና ፡ በገባለት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መሠረት ፡ ልዑል ፡ ባሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ከሰው ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ በለበሰው ፡ ሥጋ ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ ተሰቅሎ ፣ በደሙ ፡ ፈሳሽነት ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ነፃ ፡ አውጥቶ ፡ ዓለምን ፡ ከፈጠረበት ፡ ጥበቡ ፡ ይልቅ ፡ ዓለምን ፡ በአዳነበት ፡ ልዩ ፡ ጥበቡ ፡ ሲደነቅና ፡ ሲመሰገን ፡ እንደሚኖር ፡ ሁሉ ።

ይህችም ፡ የክርስቶስ ፡ አርዑት ፡ መስቀሉን ፡ የተሸከመች ፣ አሠረ ፡ ፍኖቱን ፡ የተከተለች ፡ ኢትዮጵያዊቷ ፡ እናታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሠምራ ፡ እንስታይ ፡ የጾታ ፡ ስሜት ፡ ሳያሰበረግጋት ፡ በፍጹም ፡ ቆራጥነትና ፡ ታማኝነት ፡ ፈጣሪዋን ፡ በቅርብ ፡ ሆና ፡ ለማገልገል ፡ የሚያልፈውን ፡ ዓለም ፡ በማያልፈው ፡ ዓለም ፡ ለመተካት ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ማእሰረ ፡ ፍቅር ፡ በጣጥሳ ፡ አውጭኝ ፡ እግሬ ፡ ብላ ፡ በፍና ፡ ተጋድሎ ፡ ገሠገሠች ።

ከዚያም ፣ በታላቁ ፡ ገዳም ፣ በደብረ ፡ ሊባኖስና ፡ እጅግ ፡ ታዋቂነትና ፡ ታሪካዊነት ፡ ባለው ፡ በጣና ፡ ደሴት ፡ በባሕርና ፡ በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ቆማ ፡ ንዋመ ፡ ሐኬት ፡ እንዳያገኛት ፡ በግራ ፡ በቀኝ ፡ በፊት ፡ በኋላ ፡ ሆነው ፡ እንዲጎነትሏት ፡ ጦሮች ፡ አስተክላ ፡ ስለሀገርና ፣ ስለ ሰው ፡ ደኅንነት ፡ ስትጸልይ ፡ ኖራ ፡ ከፈጣሪዋ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተቀብላ ፡ ተአምራቷና ፡ ትሩፋቷ ፡ ሲነገርላት ፡ የሚኖር ፡ ያሰመጠራጠር ፡ ተስፋ ፡ ፍጡራን ፡ ለመሆን ፡ የበቃች ፡ ሁናለች ።

